1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ " የግብር/ታክስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 30/2001 ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 35/2002 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (7) በሚከተለው ሁኔታ ተሻሽሏል።

7 ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) አፈፃፀም ወለድ የሚታሰበው ባልተከፈለው ወይም በሚቀረው የፍሬ ግብር/ታክስ የገንዘብ መጠን ላይ ነው።

3. <u>ማሻሻያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ማሻሻያ ከነሐሴ 29 ቀን 2001 ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ 2002

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር

30/2001 - 35/2002

55/2003

# የግብር/ታክስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት

# አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር

# <u>30/2001 ማሻሻያ</u>

ግብር/ታክስ በወቅቱ ባለመከፈሉ የሚታሰብ ወለድ እና በሕጎቹ ላይ የተመለከተውን ግዴታ ባለመስጠት የሚወሰነው አስተዳደራዊ መቀጫ የግብሩ አካል ሆኖ እንደሚሰበሰብ ይታወቃል።

በተለይም የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 92 ድንጋጌ ላይ አስተዳደራዊ መቀጫ እንደተወሰነ ወዲያውኑ መከፈል እንዳለበት፣ አወሳሰንና አሰባሰቡ ግብር በሚወሰንበትና በሚሰበሰብበት አፈፃፀም እንደሚመራ እና የተወሰነ ግብር የሚለው አስተዳደራዊ መቀጫንም እንደሚጨምር ተደንግጓል።

ይህንኑ መሠረት በማድረግ የክፍያ ጊዜ ከጠየቀ በርዕሱ የተጠቀሰው መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (7) ላይ ወለድ የሚታሰበው ባልተከፈለው ወይም በሚቀረው ጠቅላላ ፍሬ ግብር/ታክስ፣የወለድና የመቀጫ ድምር የገንዘብ መጠን ላይ እንደሆነ ተመልክቷል።

ይሁን እንጂ አስተዳደራዊ መቀጫ በመቀጫ አነሳስ መመሪያ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል የሚነሳ በመሆኑ፣ መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖአል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority